በዚህ መሰረት ቡድኑ ፍቃድ በወሰዱ 15 አስመጪዎች ላይ ባደረገው ምልከታ መሰረት በዋናነት

1. ወደ ሀገሪቱ የሚገባው ተሽከርካሪ ከስታንዳርድ በታች መሆኑ፣
2. አብዛኞቹ አስመጪዎች ስለተሽከርካሪው ግንዛቤ የሚሰጡበት አግባብ አለመኖሩ፣
3. ተሽከርካሪውን ከሸጡ በኋላ የጥገና አገልግሎት /After sale service/ አለመስጠታቸው፣
4. ኦሪጅናል ለሚያስመጧቸው መለዋወጫ አቅርቦት አለመኖር፣
5. ስለ ተሽከርካሪው የአደጋ ዳታ አለመያዛቸው እና ለሚከሰተው አደጋ ሃላፊነት ያለመውሰዳቸው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

በመሆኑም ቀደም ሲል በተሰራው ጥናት ላይ የተቀመጡት ምክረ ሐሳቦች መሰረት በማድረግ ከባድተሽከርካሪ አስመጪ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የአሰራር ማንዋሉን ማሻሻል በተሽከርካሪዎቹ በኩል የሚደረስው አደጋ ከመቀነስ አንጻር የራሱ ድርሻ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

በተጨማሪም አብዛኛዎቹ አስመጪዎች ድርጅቶች ፡-

1. ከአምራች ኩባንያው ወይም አምራቹ ከወከለው ህጋዊ አካል የወኪልነት ፈቃድ /Letter of Authorization/ ፣ ቻምበራይዝድ የሆነና በኢትዮጵያ መንግሥት የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ሰነድ ያላቸዉ መሆኑ፣
2. በቂ እና የተደራጀ ቢሮዎች ያላቸዉ መሆኑ፣
3. አብዛኛዎቹ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ ያላቸዉ ቢሆንም የተወሰኑት ግን በኮሚሽን ኤጀንት በኩል አቁመዉ የሚሸጡ መሆኑ፣
4. ምልከታ ከተደረገባቸዉ ዉስጥ የተወሰኑት የራሳቸዉ ጋራዥ ያላቸዉ ቢሆንም ነገር ግን አገልግሎት የሚሰጡት ለራሳቸዉ ተሽከርካሪ ብቻ እንጂ በሽያጭ ለሚያስተላልፉዋቸዉ ተሽከርካሪዎች አለመሆኑ፣
5. ከአንድ ተቋም ዉጪ ሁሉም በሚባል መልኩ መለዋወጫን እና ግንዛቤ ስልጠና (ፋሚላራይዜሽን) አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፣

6. የሽጡትን ተሽከርካሪ በተመለከተ ከሽያጭ በኋላ ምንም አይነት ዳታና ክትትል ልምድ የሌለ መሆኑ፤

በመሆኑም ከነዚህ ዋና ዋና ግኝቶችና ክፍተቶች በመነሳት የከባድተሽከርካሪ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስመጡ አስመጪዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የአሰራር ማንዋሉን እንደሚከለተው ሆኖ እንዲሻሻል ተወስኖአል፡፡

## 3.3.የከባድ ተሽከርካሪ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስመጡ አካላት በቅድሚያ ማሟላት ያለባቸው

1. የድርጅቱ ባለቤት ወይም የሥራ አስኪያጅ ሙሉ ሥም ከነአያት፣ የድርጅቱ ሙሉ አድራሻ ከተማ፣ ወረዳ፣ ክፍለ-ከተማ፣ ዞን፣ ክልል፣ የስልክ ቁጥር፣ የፋክስ እና የኢ-ሜይል የተሞላበት የማመልከቻ ፎርም፣
2. የድርጅቱ ባለቤት ወይም ስራ አስኪያጅ ብሄራዊ ዲጂታል መታወቂያ ማቅረብ ይጠበቅበታል፤
3. የድርጅቱ ባለቤት ወይም ስራ አስኪያጅ ስድስት ወር ያላለፈው ሁለት ጉርድ የፓስፖርት መጠን ያላቸው ባለከለር ፎቶ ግራፎች ማቅረብ፣
4. የድርጅቱ ባለቤት ወይም ስራ አስኪያጅ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ህጋዊ ማንነቱን የሚገልጽ ማስረጃ ዋናውን እና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ፣
5. ሕጋዊ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወይም የመጋዘን እና የመሥሪያ ቦታ ካርታ እና የባለቤትነት ማረጋገጫ ወይም ቦታው የተያዘው በኪራይ ከሆነ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት የተረጋገጠ ጊዜው ያላለፈበትሕጋዊ የኪራይ ውል ማስረጃ ማቅረብ፣
6. የተሽከርካሪ የአስመጭነት ንግድ ምዝገባ እና የግብር ከፋይ መለያ (ቲን) ቁጥር ሰርተፍኬት ዋናውን እና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ፣
7. አስመጪው ድርጅት ከአምራች ኩባንያው ወይም አምራቹ ከወከለው ህጋዊ አካል የወኪልነት ፈቃድ/Letter of Authorization/ ፣ ከሀገሩ የንግድ ምክር ቤት ቻምበራይዝድ የሆነ መረጃ፣ ወይም መረጃው የተገኘው ከኢትዮጵያ ውጪ ከሆነ ሰነዱ በኢትዮጵያ መንግሥት የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ሰነድ ዋናውን እና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ፣
8. አስመጭው ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስገባውና ለሚሸጣቸው ተሽከርካሪዎች የራሱ የሆነ የመካከለኛ እና ከባድ ተሽከርካሪ ሁለገብ ጥገና ጋራዥ ያለዉ፤

9. ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር በሚያወጣው የሰው ኃይል፣ የቢሮ አደረጃጀት፣ ቴክኒክ ማሰልጠኛና ተሽከርካሪ ማቆሚያ /ማሳያ/ ያለው፤

10. አስመጭው ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባው ተሽከርካሪ የሀገሪቱን የተሽከርካሪ ደረጃ (STANDARD) ቁጥር ES7087: 2024 መሠረት መሆን አለበት፣

11. አስመጭው ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስገባው ተሽከርካሪ በቂና አስተማማኝ የመለዋወጫ ዕቃ ማቅረብ፤

12. ለሚያስመጣቸው ተሽከርካሪ Technical Specification በእንግሊዘኛ የተፃፈ እና ሰነድ ማቅረብ፣

13. አስመጭው ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስገባው ተሽከርካሪ መንገድ ላይ ለመነዳት ብቁ ለመሆኑ (Road worthinnes Inspection Certificate) ማቅረብ፤

14. በዚህ አንቀጽ በፊደል ሀ ከ1-13 የተጠቀሱትን መስፈርቶች ተገምግመዉ ማሟላታቸዉ ሲረጋገጥ የተሽከርካሪ አስመጭነት ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ይሰጣቸዋል፡፡

15. ኮሚሽን ኤጀንት በዚህ አሰራር ማኑዋል ውስጥ አይካተቱም፤

## በአስመጪዎች መከናወን የሚገባቸው ሃላፊነት እና ግዴታዎች

1. አስመጪዎች ለሚያስመጡት ተሽከርካሪ በሽያጭ ጊዜም ሆነ ከሽያጭ በኋላ ተገቢዉ ሰነድ አሟልተዉ ለተገልጋዩ መስጠት፣
2. አዲስ ቴክኖሎጂ የተገጠመላቸዉ ተሽከርካሪዎች ሲያስገቡ ለሚያስገቧቸዉ ተሽከርካሪዎች ለተገልጋይ ሆነ ለሚመለከተው የአጠቃቀም ጥንቃቄ /ሴፍቲን/ በስፋት ማሳወቅ፣
3. አቅምን ባገናዘበ መልኩ የአዳዲስ ቴክኖሎጂን በኤግዚቢሽን /በሚዲያ/ ለሕብረተሰቡ ማስተዋወቅ፣
4. ያስመጧቸውን ተሽከርካሪዎች በሥራ ላይ ተሰማርተው ያጋጠመ ቴክኒካል ችግር መኖሩንና አለመኖሩን መረጃ መሰብሰብ፣
5. በተሽከርካሪው ላይ የተገኘ ችግር ተለይቶ ከታወቀ በኋላ ምክንያቱና መፍትሔው በሥልጠና ተካቶ ለሚመለከተው አካል ሥልጠና መሰጠት፣
6. ስለአስመጡት ተሽከርካሪዎች ቴክኖሎጂ ለሚመለከተው የሥራ ላይ ሥልጠና መስጠት፣
7. የአውቶሞቲቭን ቴክኖሎጂ መሠረት ያደረገ ከሌሎች አስመጭ ካምፓኒዎችና ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣

8. በውክልና ከሰጠው ካምፓኒው ጋር በመሆን ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ባስቀመጠው በዓመት አንድ ጊዜ ስልጠና የመስጠት፣
9. የተሽከርካሪ አስመጪ ካምፓኒዎች በየ3 ወሩ ስለተሰጠው የሥራ ላይ ስልጠና እና ያስመጧቸውን ተሽከርካሪዎች መረጃ ለትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ሪፖርት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
10. ተሽከርካሪ ወደ ሀገር ውስጥ በሚያስገቡበት ወቅት የሀገሪቱን ስታንዳርድ ያሟላ ተሽከርካሪ መሆኑን ማረጋገጥ፣
11. ለሚያስመጧቸው ተሽከርካሪዎች ዋስትና መስጠት አለባቸው፡፡

## 3.4.የቢሮ ፤ የሰው ሀይልን ፤የጋራዥ እና የመኪና ማሳያና ማቆሚያ አደረጃጀትን በተመለከተ

### 3.4.1. <u>የቢሮ አደረጃጀትን በተመለከተ</u>

1. የሥራ አስኪያጅ ቢሮ
2. የጸሐፊና የእንግዳ መቀበያ ቢሮ
3. ተሽከርካሪና የመለዋወጫ ሽያጭ
4. የሂሳቢና አስተዳደር
5. ጥራትና ቁጥጥር
6. የቴክ/ጥገናና ስልጠና

ከላይ የተገለጹትን የስራ ቦታዎች/ክፍሎች/ ለስራው አመችና በቂ በሆነ መልኩ መደራጀት አለባቸው፡፡

### 3.4.2. <u>የተሽከርካሪ የማሳያና ማቆሚያን በተመለከተ፤</u>

1. ሀገር ውስጥ ለሚገጣጥሟቸው ወይም በከፊል ለሚገጥማቸው የተሽከርካሪዎች ዓይነት
   1.1. ለ<u>2</u> ተሽከርካሪ ማቆሚያና ቢያንስ ለ <u>3</u> ተሽከርካሪ ማሳያ የሚበቃ መሆን አለበት
2. ከዋና መንገዱ ወደ ዉስጥ የሚያስገባ ከሆነ የመንገዱ ስፋት ከስድስት ሜትር የማያንስ ሆኖ
   2.1. ቢያንስ በጠጠር የተሰራ መሆን አለበት